# አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ.)
# LION INSURANCE COMPANY (S.C.)

## ለአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ.
## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት
## ዕጩዎች ጥቆማ ለመቀበል የወጣ ማስታወቂያ

የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቋማዊ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር ኤስ.አይ.ቢ/48/2019 መሰረት በ17ኛ የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የቦርድ አባላት ምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት መርጧል፡-

በዚህም መሰረት የምልመላ እና አስመራጭ ኮሚቴው ከባለአክስዮኖች የሚቀርብለትን የቦርድ አባላት ዕጩዎች ጥቆማ ለመቀበል የሚያስችለው ዝግጅት ያጠናቀቀ ስለሆነ፤ ለቦርድ አባልነት የሚያስፈልገውን መስፈርት የሚያሟሉ ዕጩዎችን **ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2018 ዓ.ም** ባለው ጊዜ ውስጥ ከባለአክስዮኖች ጥቆማ የሚቀበል መሆኑን ያሳውቃል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር ኤስ.አይ.ቢ/48/2019 እና ኤስ.አይ.ቢ/32/2012 መሠረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባልነት የሚጠቆሙ ዕጩ አባላት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

1. የኩባንያው ባለአክስዮን የሆነ/ች፣
2. ዕድሜ 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ/ች፣
3. በማንኛውም ኢንሹራንስ ኩባንያ ሠራተኛ ያልሆነ/ች፣
4. በማንኛውም የፋይናንስ ተቋም የቦርድ አባል ያልሆነ/ች፣
5. የኩባንያው አስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆነ/ች፣
6. ሀቀኛ፣ ታማኝ እና መልካም ዝና ያለው/ያላት፣
7. ቦርዱ በቂ የፆታ፣ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ስብጥር ያለው እንዲሆን ለማስቻል ተጠቋሚ ዕጩው/ዋ ቢያንስ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ኖሮት/ኖሯት በኢንሹራንስ፣ በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በህግ፣ በንግድ ሥራ አስተዳደር፣ በኦዲት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ እና በኢንቨስትመንትና ፕሮጀክት ማኔጅመንት የሙያና የሥራ ዘርፎች ልምድ ያለው/ያላት ቢሆን ይመረጣል፣
8. በኢትዮጵያ እና ከኢትዮጵያ ውጪ በማጭበርበር፣ ዕምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ/ሳ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት/ተሰጥቶባት የማያውቅ/የማታውቅ፣
9. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት/ያልቀረበባት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት/ባት፣
10. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት ንብረቱ/ቷ በሐራጅ ጨረታ ያልተሸጠበት/ባት፣ ተከሶ/ሳ ያልተፈረደበት/ባት ወይም እሱ የሚመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት/የሆነችበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ ብድር ያልዞረበት/ባት ወይም ያልገባበት/ባት፣
11. በቂ ስንቅ ገንዘብ ሳይኖር ቼክ በመስጠቱ ሂሳቡ ያልተዘጋበት/ባት፣
12. ግብር ባለመክፈል ተከስሶ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ያልተባለ/ች፣
13. የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በዕጩነት ሊጠቆም ይችላል፣
14. ከሚጠቆሙት 18 ዕጩዎች መካከል 1/3ኛ (ስድስቱ) የሚጠቆሙት ከኩባንያው ጠቅላላ አክስዮን ከ2% በታች ድርሻ በያዙና ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች (Non-Influential Shareholders) ነው፣
15. ቀሪዎቹ 2/3ኛ (አስራ ሁለቱ) ዕጩዎች በሁሉም ባለአክስዮኖች በጋራ የሚጠቆሙ ናቸው፡፡
16. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ላይ የተገለጹ ሌሎች መመዘኛዎችን የሚያሟላ/የምታሟላ፡፡

**ስለሆነም የኢንሹራንስ ኩባንያው ባለአክስዮኖች ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎችን በሚከተሉት የጥቆማ መቀበያ መንገዶች በመጠቀም በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቆማችሁን ለአስመራጭ ኮሚቴው እንድታቀርቡ ተጋብዛችኋል፡፡**

➢ **የጥቆማ መቀበያ መንገዶች፣**

1. በአንበሳ ኢንሹራንስ ሕንፃ (ዋና መ/ቤት) 2ኛ ፎቅ ፋይናንስና ኢንቨስትመንት መምሪያ በአካል በመቅረብ በተዘጋጀው ቅፅ በመሙላት፣
2. በፖስታ ሳጥን ቁጥር 26281/1000 በመላክ፣ ወይም
3. ለዚሁ ተግባር በሁሉም የኩባንያው ቅርንጫፎች የተቀመጡ ቅፆችን ሞልቶ እና ፈርሞ ለቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ ወይም ለሚወክለው ሰው በማስረከብ ጥቆማ መስጠት ይቻላል፡፡ ወይም በኢሜልnominationcommittee@anbessainsurance.com አድራሻ መላክ ይቻላል፡፡
4. በተጨማሪም ለባለአክስዮኖች መጠቆሚያ የተዘጋጀው ቅፅ ከኩባንያው ዌብሳይት www.anbessainsurance.com በማውረድ ቅፁን ሞልቶ በኩባንያው የእንግዳ መቀበያ በተዘጋጁ ሳጥኖች ውስጥ በማስገባት መመለስ ይቻላል፡፡
5. ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር +251911066350 ወይም +251911195698 መደወል ይቻላል፡፡

**የአንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አ.ማ.**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ ምልመላ እና ምርጫ ኮሚቴ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ**

**በአገልግሎቱ የሚረኩበት፣ በጥንካሬው የሚመኩበት!!**
**For Rellable Service and Dependable Capacity!!**